የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር ኸ/1162/8/817
ቀን ታሕሣስ 18 2015

**ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ፓርቲ**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ፓርቲ በታህሳስ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በቁጥር አብን 240/04/15 ለቦርዱ በተጻፈ አቤቱታ ከዚህ ቀደም ቦርዱ ለፓርቲው በጻፈው ደብዳቤ የካቲት 14-15 ቀን 2012 ዓ.ም ፓርቲው በደብረብርሃን ከተማ ያካሄደውን 2ኛ መደበኛ ጉባኤና ውጤቱን ያላጸደቀ መሆኑን፤ ቦርዱ እውቅና የሚሰጠው ሰኔ 3 ቀን 2010 ዓ.ም የጸደቀውን የፓርቲውን ህገ-ደንብ፤ ብሔራዊ ምክር ቤት እና ሌሎች የፓርቲው አካላትን ብቻ እንደሆነ ማሳወቁ አግባብነት እንደሌለው ገልጸ ስራ አመራር ቦርዱ ጉዳዩን መርምሮ የእርምት ውሳኔ እንዲሰጥልን ሲል አመልክቷል።

ቦርዱም ፓርቲው ያቀረበውን አቤቱታ ከህጉ እና ከፓርቲው ሰነዶች አንጻር መርምሯል። እንደሚታወቀው ፓርቲው በየካቲት 14-15 ቀን 2012 ዓ.ም በደብረብርሃን ከተማ ካደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ጋር ተያይዞ ፓርቲው ያስተላለፋቸው ውሳኔዎችም ሆኑ የተመረጡት የፓርቲው የተለያዩ አመራር አካላት ጉባኤው በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት ባለማሟላቱ ቦርዱ እንዳልተቀበለው ለፓርቲው ገልጸለት የተጓደሉ የተባሉ ነጥቦችን አሟልቶ ጉባኤ እንዲያደርግ በመስከረም 12 ቀን 2013 ዓ.ም እና በሚያዝያ 15 ቀን 2013 ዓ.ም ቦርዱ አሳውቋል።

ከዚህ በኃላም ቦርዱ ሰኔ 2013 ዓ.ም እና መስከረም 2014 ዓ.ም ለተደረገው አገራዊ ምርጫ የተለያዩ ክንዋኔዎችን ሲመራና ውሳኔ ሲያስተላልፍ የቆየበትና ከፍተኛ የሥራ ጫና ያስተናገደበት ጊዜ ከመሆኑ አንጻር ቦርዱ ለፓርቲው የሰጠውን መመሪያ ተከታትሎ ሳያስፈጽም መቆረቱን ቦርዱ ተገንዝቧል። በዚህም ምክንያት ፓርቲው



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

በደብረብርሃን ያደረገው ጉባኤ ውጤት የሆኑት የፓርቲው ደንብ እና በጉባኤው የተመረጡ አመራር አካላት ስራቸውን በመቀጠል ከቦርዱ ጋር የሚያገናኛቸውን ተግባራት በሙሉ ሲያከናውኑ ቆይተዋል። ይህም ለስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ዕጩ ማቅረብ እና በምርጫ መወዳደር፤ ከቦርዱ ለፓርቲዎች የሚሰጥን የገንዘብ ድጋፍ መቀበልና የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ እና ፓርቲውን ወክሎ ከቦርዱ ጋር ግንኙነቶችን ማድረግን ያካትታል።

ከዚህ አንጻር አሁን በስራ ላይ ያለው እና በደብረብርሃኑ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡት የፓርቲው  አመራር አካላት እውቅና አለመስጠት ፓርቲው ለሶስት አመታት ያከናወናቸውን ተግባራት ዋጋ አልባ የሚያደርግ መሆኑን ቦርዱ በመገንዘብ እንዲሁም የፓርቲውን ሕልውና ለማስቀጠል ሲባል ቦርዱ በታህሳስ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በቁጥር አ1162/11/812 ለፓርቲው የጻፈው ደብዳቤ ላይ ማስተካከያ በማድረግ የደብረብርሃን ጉባኤ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎችም ሆኑ የውሳኔዎቹ ውጤቶች ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል ሲል የማስተካከያ ውሳኔ ሰጥቷል።

በሌላ በኩልም ፓርቲው በቀጣይ ሊጠራው ስለሚገባው ጠቅላላ ጉባኤ ሊከተላቸው የሚገቡ ሁኔታዎች ላይ ቦርዱ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል።

1. ፓርቲው አሁን በሚያከናውነው ጉባኤ ላይ ሊሳተፉ የሚገባቸው የጉባኤ አባላት በፓርቲው የባህር ዳር ጉባኤ ላይ የተሳተፉ የጉባኤ አባላት መሆን እንዳለባቸው፤  እንዲሁም በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በወቅቱ ያልተካተቱ ወይም በባህርዳሩ ስብሰባ ላይ ተገኝተው አሁን መገኘት በማይችሉት ምትክ ሌሎችን በመተካት ተሰብሳቢዎችን መጥራት ያለበት መሆኑን፤
2. በፓርቲው ጉባኤ ላይ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን በተመለከተ ቦርዱ ከዚህ ቀደም ለፓርቲው በደብዳቤ በገለጸው መሰረት አንዱ አጀንዳ የሆነው "የሪፎርም ሰነድ" ለጉባኤ የሚቀርብበትን አግባብ በዝርዝር እንዲያዘጋጅ፤ በተጨማሪም የፓርቲው የሚሻሻለው ደንብና ሌሎች ተጨማሪ የሚቀርቡ አጀንዳዎች (ካሉ)

ዝርዝሩን በቅድሚያ በማዕከላዊ ኮሚቴ አስወስኖ ለቦርዱ ሊያቀርብ የሚገባ መሆኑን፤

3. በመጨረሻም የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ከላይ የተገለጹት ነጥቦች ላይ ስብሰባ በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ ፓርቲው ለቦርዱ በቅድሚያ እንዲያሳውቅ እና የቦርዱ ተወካይ በስብሰባው ላይ እንዲገኝ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ቦርዱ ወስኗል።

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርፍ

ውብሸት አየለ ገጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board